አዘጋጅ ናስሪን ዚገ

# ደንሺ ሳሮን ደንሺ

## እና ሌሎችም የህፃናት ታሪኮች



Art of Buna

Art of Buna

GOETHE INSTITUT

Art of Buna

የወጥ ስራው ባለመብት
የጀርመን ባህል ተቋም፡፡ © 2006 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

ይህ ህትመት ©2010 በጀርመን ባህል ተቋም ፈቃድ በአርት ኦፍ ቡና አማካኝነት የወጣ ነው፡፡
አዘጋጅ፣ ናስሪን ዚገ
ስዕል፣ ረዳት ፕሮፌሰር ጌታቸው ዮሴፍ
አስተባባሪ፣ ዮናስ ታረቀኝ
የሽፋን ዲዛይንና ኢሉስትሬሽን፣ አና-ካትሪን ሃን እና ጊኖ ፋግሊኖ፣
ሌይ አውት፣ ቶማስ በርግሃውስ

# ዱንሺ ሳሮን ዱንሺ

## እና ሌሎችም የህፃናት ታሪኮች

አዘጋጅ ናስሪን ዚገ

ህትመት አርት ኦፍ ቡና

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ንፋስን መያዝ | 9 |
| የቤተሰብ ቀን | 13 |
| ትናንሾቹ የጫካው ጠባቂዎች | 21 |
| ስግብግቡ ጀብና ብልጧ አህያ | 25 |
| ድንቡሼ እና ጓደኞቹ | 29 |
| የጉንዳኖቹ ሀገር | 33 |
| ደንሺ ሳሮን ደንሺ | 37 |
| ቦቢ የት ነህ? | 43 |
| ሊስትሮው አብዲ | 47 |
| መልካሙ ቁራ | 53 |
| የተረሳው ጭቅጭቅ | 57 |
| የሚሹ ድመት | 63 |
| ከረሜላዬ | 69 |
| ቀበሮ ለምን የጫካ አይጥ እንደሚበላ | 73 |

# ንፋስን መያዝ

ከዳንኤል ነጋሽ ዋጋዬ

ሮዳስ፣ ማህደር እና ጤናዬ ጓደናሞች ናቸው፡፡ አንድ ላይ መጫወት ደስ ይላቸዋል፡፡ ዛሬ የሚጫወቱት ገመድ ዝላይ ነው፡፡ ሁሉም በየተራ ይጫወታሉ፡፡ ገመዱም ወደ ላይ ከፍ ተደርጎ ትከሻ ድረስ ተይዟል፡፡

በመጀመሪያ ተረኛ የነበረችው ማህደር ነበረች፡፡ ግን እዚያ ከፍታ ድረስ መዝለል አልቻለችም፡፡ ሮዳስ ግን በቀላሉ ዘለለችው፡፡

“ፎርሽሻል! ገመዱን በእግርሽ ነክተሻል!” በማለት ማህደር ተናገረች፡፡

“አልነካሁም!” ሮዳስ በቁጣ መለሰች፡፡

“ነክተሻል!” ማህደር ወደ ጤናዬ ዞራ “አንቺም አይተሻል አይደል!” አለቻት፡፡

“እኔ እንጃ...” ጤናዬ የምትመልሰው ጠፋት፡፡

“አየሽ! አንቺ መዝለል ስላቃተሽ ነው የምታፍሪው!” አለቻት ሮዳስ በቁጣ፡፡ ሁሉም ተናደው ተበታተኑ፡፡

ከሰዓት በኋላ አሻንጉሊቶቻቸውን ይዘው ሲጫወቱ ተገናኙና እንደገና አብረው መጫወት ጀመሩ፡፡

“ንፋስን መያዝ እችላለሁ!” አለች ሮዳስ በድንገት፡፡

“እንዴት አድርገሽ? የማይሆን ነገር ነው” አለች ጤናዬ ተኮሳትራ፡፡

“እንወራረድ?” ሳቀች ሮዳስ፡፡

“ንፋስን መያዝ አይቻልም፡፡ አብደሻል መሰለኝ!” ማህደር እራሷን ነቀነቀች፡፡

“እሺ እዚሁ ጠብቁኝ!” አለችና ሮዳስ ወደ ቤቷ ሮጣ ገብታ ቢራቢሮ መያዣ መረብ ይዛ መጣች፡፡ ‹በእዚህ ቢራቢሮዎቹን ስይዝ ንፋሱንም አብሬ እይዘዋለሁ› ብላ አሰበች፡፡

ሮዳስ አንድ የከንፎቹ ቀለማት ደማቅ የሆነ ቢራቢሮ ስታባርር ማህደርና ጤናዬ ተመለከቷት፡፡ ሮዳስ ቢራቢሮውን ያዘችው፡፡ ንፋሱን ግን ልትይዘው አልቻለችም፡፡

ቢራቢሮውን ለቀቀችውና ተመልሳ ወደ ቤቷ ሮጣ ሄዳ ፊኛ ይዛ መጣች፡፡

“ቆይ በዚህ ስይዘው አሳያችኋለሁ” አለቻቸውና በጉጉት እሚመለከቷት ጓደኞቿ ፊት ሮዳስ ፊኛውን መንፋት ጀመረች፡፡ ፊኛው ትልቅ እየሆነ ሄደ፣ ሄደ ሄደና ... ፈነዳ! ልክ ሲፈነዳ ጤናዬ ድንግጥ አለች፡፡ ማህደር ሳቀች፡፡ ሮዳስ ተናደደች፡፡

“በይ ይብቃሽ! ንፋስን ማንም ሊይዘው አይችልም፡፡ ትልቅም ሰው ቢሆን



እንኳን” አለቻት ማህደር ልታፅናናት፡፡

“እንደምይዘው እርግጠኛ ነኝ! አሳያችኋለሁ!” ብላ ሮዳስ ወደ እናቷ ሄደች፡፡ እናቷ ሰዓሊ ነች፡፡ ትልቅ፣ ደማቅ ቀለማት ያሉት ስዕል እየሳለች ነበር፡፡

“እማዬ በአስቸኳይ የውሃ ቀለም፤ ብሩሽ እና የስዕል መሳያ ወረቀት ስጪኝ” አለቻት ሮዳስ፡፡

“ስዕል ልትስዪ ነው?” አለቻት እናቷ ደስ እያላት፡፡

“አዎን! ማለቴ ከማህደር እና ጤናዬ ጋር ንፋሱን እይዘዋለሁ ብዬ ተወራርጃለሁ” በማለት ነገረቻት፡፡

“ለሱ ነው ቀለሞች፣ ብሩሽ እና የስዕል ወረቀት የፈለግሺው?”

“አዎን ንፋሱን ለዘላለም እይዘዋለሁ!”

“እስቲ በይ አሳዪኝ! እኔም ስትይዢው ለማየት በጣም ነው የቸኮልኩት...”

ሮዳስ እናቷ አስተያየት እየሰጠቻት መሳል ጀመረች፡፡ ከእናቷ ጋር ብዙ ጊዜ የምትሄድበትን መናፈሻ ሳለችው፡፡ ለእናቷ ስዕሉን እያሳየች፤ “እነዚህ ትላልቆች ዛፎች ናቸው፡፡ እዚህ ጋ የምታዪው ንፋሱ ቅርንጫፎቹን ሲያወዛውዝ ነው፡፡ እነዚህ ከዛፉ ላይ የረገፉ ቅጠሎች ናቸው፡፡ ንፋሱ ስለሚያንሳፍፋቸው በአየሩ ውስጥ እየበረሩ ነው፡፡”



“አዎን ንፋሱ በደንብ ይታየኛል! ንፋሱን ለዘላለም ይዘሽዋል!” እናቷ በጣም ተደነቀች፡፡

ሮዳስ ለማህደር እና ለጤናዬ አሳየቻቸው፡፡

“ንፋሱን አየሁት!” አለች ማህደር፡፡

“እኔም!” አለች ጤናዬ፡፡

“እኔም ንፋሱን መያዝ እፈልጋለሁ!” አለች ማህደር፡፡

“እኔም!” አለች ጤናዬ፡፡

የሮዳስ እናት ብሩሽ፣ ቀለም እና ወረቀት ሰጠቻቸው፡፡ ሮዳስ ከጓደኞቿ ጋር ቁጭ ብላ ንፋሱን ለመያዝ እንዴት እንደሚስሉ ማየት ጀመረች፡፡



# የቤተሰብ ቀን

ከዳንኤል ወርቁ

ኬሲ ክፍሏ ውስጥ እየተጫወተች እያለ እናቷ "ኬሲ! ኬሲ!" እያለች በተደጋጋሚ ጠራቻት፡፡

"ምንድን ነው?" ስትል ኬሲ ቆይታ መልስ ሰጠች፡፡

"አባትሽ ዛሬ ሊወስድሽ እንደሚመጣ እንዳትረሺ! ቶሎ ቶሎ ተዘጋጂ፡፡

እንደመጣ ወዲያውኑ ይዞሽ እንደሚሄድ ነግሮኛል፡፡ እስክትዘጋጂ መጠበቅ አይችልም፡፡ ጊዜ የለውም" በማለት እናቷ አስታወሰቻት፡፡

"ሰማህ አይደል? እኔም የማስበው እንዲሁ ነው፡፡ ሁሌም እንደተጣደፈ ነው" ስትል ኬሲ ክፍሏ ውስጥ እንዳለች ዝግ ባለ ድምፅ ተናገረች፡፡

"ተዘገጃጂ!" አለቻት እናቷ በድጋሚ፡፡

"አባቴ ይወደኛል ብለህ ታስባለህ?" አሁንም ኬሲ ክፍሏ ውስጥ እንዳለች ወደ መስኮቱ በኩል ዞራ በሹክሹክታ ተናገረች፡፡ መልስ የምትጠብቅ አይመስልም፡፡

ጆሮዋን ወደ መስኮቱ አድርጋ አዳመጠች፡፡

"ልክ ነህ! አባቶች ልጆቻቸውን ይወዳሉ፡፡ እሱን አውቃለሁ፡፡ እኔ የምልህ ግን አባቴ እኔን ይወደናል ብለህ ታስባለህ ወይ ነው?"

"ከማን ጋር ነው የምታወሪው ኬሲ?" ስትል እናቷ የኬሲ ክፍል በር ላይ ቆማ ጠየቀቻት፡፡



"ከጓደኛዬ ጋር!" ኬሲ መለሰች፡፡

"ከየት የመጣ ጓደኛ?" እናቷ ግራ በመጋባት ክፍሉ ውስጥ ገብታ



ተመለከተች፡፡

"እስካሁን ተዘጋጅተሽ አልጨረሽም! አባትሽ አሁን ይመጣል" አለቻት፡፡

ኬሲ አንገቷን ነቀነቀችና ወደ መስኮቱ አቅጣጫ ተመልክታ በድንገት ሳቋን ለቀቀችው፡፡

"ምን ሆነሻል! ለመሆኑ ደህና ነሽ?" እናቷ በጭንቀት እያየቻት ጠየቀቻት፡፡

"በፎፊ ምክንያት ነው የምስቀው ማሚ! ፎፊ እኮ ነው ዝም ብሎ ሚያስቀኝ፡፡"

"ማነው እሱ ፎፊ?"

"ጓደኛዬ ነዋ!"

"ጓደኛሽ እዚህ ቤት ውስጥ አለ?"

"አዎን ያውልሽ እዚያጋ እኮ...!"

"እዚህ ካለ እኔ እንዴት አላየውም?" አለች እናቷ ግራ ተጋብታ፡፡

"እሱን ማየት የምችለው እኔ ብቻ ስለሆንኩ!"

"እንደሱ ነው በይ አሁን ፍጠኚ!" አለቻት እናቷ ጭንቅላቷን እየነቀነቀች፡፡

"ከአባዬ ጋር አልሄድም!"

"ምን አልሽ?"

"ዛሬ ከአባዬ ጋር አልሄድም አልኩሽ!"

"እኮ ለምን?... እምቢ ስትዪው ሃዘን እንደሚሰማው ታውቂያለሽ አይደል"

"ውሸትሽን ነው! እኔ ግን ምንም ...!"

በዚህን ጊዜ ስልኩ ደወለ፡፡ አባትየው ነበር የደወለው፡፡ ኬሲ ከእሱ ጋር መሄድ እንደማትፈልግ ሲሰማ ኬሲ እራሷ እንድታናግረው እንደሚፈልግ ተናገረ፡፡ ኬሲ ግን በስልክ ልታናግረው እንደማትፈልግና እሷን ማናገር ከፈለገ እዚህ ድረስ መምጣት እንዳለበት ለእናቷ ነገረቻት፡፡

"ለማናገር ብሎ እዚህ ድረስ እንደማይመጣ ታውቂለሽ፡፡"

"እንደዛ ከሆነ ከእሱም ጋር ካንቺም ጋር መነጋገር አልፈልግም፡፡"

የኬሲ እናት በነገሩ ግታ ተጋብታ ከኬሲ ክፍል ወጥታ ወደ ስልኩ በመሄድ ከተነጋገረች በኋላ ወደ ኬሲ ክፍል ተመልሳ መጥታ አባቷ እታች ሳሎን ቤት እየጠበቃት መሆኑን ነገረቻት፡፡

ኬሲ ፊቷ በፈገግታ ተሞልቶ ለአባቷ ሰላምታ አቀረበች፡፡ ሶፋው ላይ ቁጭ

ሲል ሲል ኬሲ ድንግጥ ብላ "አባባ ቆይ እሱጋ አትቀመጥ!" አለችው፡፡

"ለምን!?" ዘሎ ተነሳና ባዶውን ቦታ ተመለከተው፡፡

"እሺ የኔ ቆንጆ የት መቀመቀጥ እንዳለብኝ ንገሪኝ!"

ኬሲ ቀደም ሲል ሊቀመጥበት የነበረበትን ሶፋ አመለከተችውና "ጓደኛዬ ላይ ተቀምጠህበት ነበር እኮ!" አለችው፡፡



"የታል ለመሆኑ ማን ይባላል?"

"ፎፊ ይባላል፡፡ አያቴን ነው የሚመስለው ... ትላልቅ ጆሮዎችና አስቂኝ ፊት አለው፡፡"

"እንደምን ዋልክ ፎፊ!" በማለት አባትየው ለማይታየው ፎፊ ሰላምታ አቀረበ፡፡ "ጓደኛሽ ይወደኛል?" ሲል ጠየቃት፡፡

"አይወድህም" አለች ኬሲ ኮስተር ብላ፡፡

"ለምን?" አባቷ በመገረም ጠየቃት፡፡

"ማን እንደሆንክ ስለማያውቅ ነዋ!"

"ማን እንደሆንኩ ታዲያ ለምን አትነግሪውም?"

"እኔም አንተን ስለማለውቅህ ነዋ!"

"ምን ማለትሽ ነው ኬሲ?" አባትየው ደነገጠ፡፡



"አትናደድ! እውነቴን ነው፡፡ ማን እንደሆንክ እኮ በትክክል አላውቅም...፡፡ ባለፈው ሳምንት አስተማሪያችን ስለአባቶቻችን እንድንጽፍ አዛን ነበር፡፡ እኔ ምንም ያልተፃፈበት ወረቀት ሰጠኋት፡፡ ለምን ስላንተ እንዳልፃፍኩ ጠየቀችኝ፡፡

እኔም ማንና እንዴት አይነት አባት እንደሆንክ እንደማላቅ ነገርኳት፡፡ አስተማሪያችንም እናቴን እንድጠይቃት ነገረችኝ፡፡ ማሚን ስጠይቃት እሷም ማን እንደሆንክ እንደማታውቅ ..."

የኬሲ አባት ምን መናገር እንዳለበት ግራ ገባው፡፡ ልጁን እያየ እንባ ሲተናነቀው ታወቀው፡፡ በመጨረሻም፤ "እኔ አባትሽ ነኝ! ደግሞም በጣም እወድሻለሁ!" በማለት ሃዘን በተቀላቀለበት ድምፅ ተናገረ፡፡

"አውቃለሁ! ግን እኔ ስፈልግህ አንተ አትገኝም፡፡ በሳምንቱ መጨረሻ መጥተህ ስትወስደኝ እንኳን ሁሌ እንደተጣደፍክ ነው፡፡ ከእኔ ጋር ስትሆን በፍፁም አታጫውተኝም፡፡"

"በቃ ... ጥሩ አሁን ሁሉም ነገር ገብቶኛል እንሂድ!"

ኬሲ ፎፊ ወደተቀመጠበት ሶፋ ተመለከተች፡፡ ጀርባዋን ለአባቷ ሰጥታ "የትም አልሄድም!" ስትል ተናገረች፡፡

"ለምን?"

"ፎፊ አትሂጂ ብሎኛል!"

"ማንን ነው የምትሰሚው? አባትሽን ነው ወይስ ማንም ሊያው የማይችለውን ጓደኛሽን?"

"እሱ የኔ ጓደኛ ብቻ አይደለም፡፡ አያቴም ነው፡፡ አያቴን ነው የሚመስለው፡፡ ስፈልገው ሁሌም ከእኔ ጋር ይሆናል፡፡ አያቴ ያወራልኝ እንደነበረው ተረት ያወራልኛል፡፡ ያስቀኛል፡፡ ከእኔ ጋር ይጫወታል፡፡ በኔ ምክንያት እንዲያዝን አልፈልግም፡፡?"

አባቷ ተመልሶ ተቀመጠ የልጁን እጅ ያዘና ኮስተር ባለ ድምፅ "ፎፊን ይዘነው ብንሄድ ምን ይመስልሻል?" ሲል ጠየቃት፡፡

ኬሲ ወደ ሶፋው ተመለከተችና ትንሽ ቆይታ "ከእኛ ጋር መሄድ አይፈልግም፡፡"

“ታዲያ ምንድን ነው የሚፈልገው?”

“ቃል እንድትገባለት ነው የሚፈልገው...”

“ምን ብዬ?”

“የምለምንህን ነገር ሰምተህ እንድትፈፅምልኝ፡፡”

“እሺ ቃል እገባልሻለሁ!”

ኬሲ የማይታው ጓደኛዋ ወዳለበት ሶፋ ተመለከተች፡፡

“ፎፊ እና እኔ ማሚ አብራን እንድትሄድ እንፈልጋለን” አለች ትንሽ ቆይታ፡፡

አባቷ ቶሎ ብሎ መልስ አልሰጠም፡፡ ቆየት ብሎ ግን እናትሽ እሺ ካለች እስማማለሁ አላት፡፡ ኬሲ አባቷን ሳመችውና ወደ እናቷ መኝታ ቤት ሮጠች፡፡ እናቷ አልጋ ላይ ጋደም ብላ መጽሐፍ እያነበበች ነበር፡፡

“ማሚ ተነሺ እንሂድ!”

“የት ነው የምንሄደው?” እናቷ ግራ ተጋብታ ጠየቀቻት፡፡

“ከአባቢ ጋር!” እናቷ እራሷን ነቀነቀችና ወደ ንባቧ ተመለሰች፡፡

“ማሚ እየጠበቅኩሽ እኮ ነው!”

“ታውቂያለሽ እኔና አባትሽ እንደ ...”

“አዎን! አውቃለሁ ማሚ! ከእናቴና አባቴ ጋር አብሬ መሄድ እንደምፈልግም አውቃለሁ!”

“አባትሽ ምን አለ?”

“እሱ ተስማመቷል!”

“እንዴት ሊስማማ ቻለ ... ?”

“ፎፊ አባትሽን ጠይቀው አለኝ፡፡ ስጠይቀው ጊዜ እሺ ብሎኝ ሁላችንም አብረን እንድንሄድ ተስማማ፡፡”

“ጓደኛሽ የት ነው ያለው? አንድ ጊዜ ልሳመው!” አለችና እናቷ ፈገግ ብላ ልብሷን መቀየር ጀመረች፡፡

“ፎፊ ነግሬህ አልነበርም! አባቴን ትወደዋለች አላልኩህም! እንዴት እንደተደሰተች አየህ?” አለች ኬሲ፡፡

ኬሲ እና እናቷ አብረው ኬሲ አባት ወደተቀመጠበት ሳሎን ሄዱ፡፡ ቀና ብሎ የቀድሞ ሚስቱን ተመለከታት፡፡



“በጣም ታምሪያለሽ!” አላት፡፡

“አመሰግናለሁ!” አለችው፡፡

ኬሲ የወላጆቿን እጆች ያዘችና “ማሚና አባቢ! አሁንም ፎፊ አንድ ነገር እንድለምናችሁ እየነገረኝ ነው፡፡”

“ምን ብሎ?” ሁለቱም አንድ ላይ ጠየቋት፡፡

“ቅዳሜ ቅዳሜ የቤተሰብ ቀን ይሁን” ወላጆቿ ተያዩ፡፡ አንዳቸውም ግን ምንም አልተናገሩም፡፡

“ምነው ይህን ያህል ከባድ ነገር ነው?” ስትል ጠየቀች ኬሲ፡፡



እናትና አባቷ ተያዩና አንገታቸውን ነቀነቁ፡፡ በዚህን ቀን የቤተሰብ ቀኑ ተጀመረ፡፡

# ትናንሾቹ የጫካው ጠባቂዎች

ከሺበሺ ለማ

ከሰዓት በኋላ አመሻሽ ላይ ነው፡፡ የወረቦ መንደር እረኞች በጎቻቸውን፣ፍየሎቻቸውን እና ላሞቻቸውን ወደ ሰፈራቸው እየነዱ እየተመለሱ ነበር፡፡



ከእረኞቹ አንዱ የሆነው ዲኖ በኩራት አህያውን እየጋለበ ነው፡፡ በድንገት ሁለት አስፈሪ ሰዎች የእረኞቹን መንገድ ዘጉባቸው፡፡ ቀስትና ማስወንጨፊያ ይዘዋል፡፡ በትከሻዎቻቸው ደግሞ ጆንያዎች ተሸክመዋል፡፡

“አንተ! ከአህያው ላይ ውረድ!” አሉት ዲኖን፡፡

ዲኖ በፍርሃት ተውጦ ከአህያው ላይ ወረደ፡፡ ዲኖ እና ሌሎቹ እረኞች ሰዎቹ ጆንያዎቹን አህያው ጀርባ ሲጭኑ ልብ ብለው ተመለከቷቸው፡፡

“ዝም ብላችሁ ወደ ቤታችሁ ሂዱ፣ ለአንድ ሰው ብትናገሩ ወዮላችሁ!” ብለዋቸው አህያውን እየገረፉ በመንዳት ወደ ከለዌ ጫካ አቅጣጫ ሄዱ፡፡

“አህያዬን ሰረቁብኝ፣ ለአባቴ አሁን ምን ብዬ ነው የምነግረው?” አለ ዲኖ እያለቀሰ፡፡

“ምንም ማድረግ እንዳልቻልክ ለአባትህ ንገራቸዋ!” አለ አንዱ እረኛ፡፡

“እንደሱማ አይሆንም፡፡ ቆይ! የማደርገውን እኔ አውቃለሁ፡፡ አህያዬን መልሼ አመጣዋለሁ!” አለና ከብቶቹን የሚያግድበትን ዱላ በመያዝ ለመሄድ ተነሳ፡፡

“እኔም ካንተ ጋር እሄዳለሁ!” አለውና ጓደኛው ሲሳይ አብረው ሆነው



ዘራፊዎቹን ተከተሏቸው፡፡

ዲኖ እና ሲሳይ ሰዎቹ የሚያደርጉትን ለማየት በጣም የጓጉ ቢሆንም ትንሽ ትንሽ መፍራታቸው ግን አልቀረም፡፡ እየጨለመ ሄደ፡፡ ቀስ ብለውና ድምፃቸውን አጥፍተው እስከ ከለዌ ጫካ ተከተሏቸው፡፡ ረዣዥሞቹ ሳሮች ውስጥ ተደብቀው ሰዎቹ የሚደርጉትን መመልከት ጀመሩ፡፡ አህያውን ገላጣው ስፍራ ላይ ካለው ዛፍ ጋር አሰረው፣ መሳሪያቸውን ተሸክመው ሲሄዱ ወደ ጫካው ዳር ቀረብ፣ ቀረብ ሲሉ ተመለከቷቸው፡፡

“ህገ ወጥ አዳኞች ናቸው ማለት ነው!” ሲል ዲኖ በሹክሹክታ ተናገረ፡፡

“በል አህያውን እንፍታና ወደ ቤታችን እንሂድ” አለ ሲሳይ፡፡

“አይሆንም! የዱር እንስሳ ሲገድሉማ ዝም ብለን ማየት የለብንም!” አለው ዲኖ እራሱን እየነቀነቀ፡፡

ብዙም ሳይቆይ ሶስት ድኩላዎች ወደ ገላጣው ስፍራ መጡ፡፡ ድኩላዎቹ አረንጓዴውን ሳር መንጨት ጀመሩ፡፡ አንዱ ድኩላ ደግሞ ጀርባውን አንድ ቋጥኝ ላይ ማከክ ጀመረ፡፡

አዳኞቹ መሳሪያውን ይዘው ቀስ እያሉ ወደ እንስሳቱ ሲጠጉ ዲኖና ሲሳይ ተመለከቷቸው፡፡

ሲሳይ አንድ ድንጋይ አነሳና በኃይል ወርውሮ ከቋጥኙ ጋር አጋጨው፡፡



“ቅዋ! ! !” የሚል ኃይለኛ ድምፅ ተሰማና እሳት የመሰለ ብርሃን ብልጭ አለ፡፡

በዚህን ጊዜ እንሰሳቱ ደንግጠው በኃይል እየዘለሉ ጥቅጥቅ ወዳለው ጫካ ገቡ፡፡

“የጫካዎቹ ጠባቂዎች ናቸው፡፡ ሩጥ እናምልጥ! ከያዙን ያስሩናል!” አለ አንዱ ሰውዬ ከዚያም በሚችሉት ሁሉ በፍጥነት ሮጡ፡፡

ዲኖና ሲሳይ አህያቸውን እየፈቱ ቀስ ብለው ሳቃቸውን ለቀቁት፡፡

“የጫኑትን ጆንያ ምን እናድርገው? እዚህ ጥለነው እንሂድ?” በማለት ሲሳይ ጠየቀ፡፡

“ለጫካው ጠባቂዎች ብንሰጣቸው ይሻላል” አለ ዲኖ፡፡

እየሳቁ መንደራቸው ሲደርሱ፤ በጓደኞቻቸው የጀግና አቀባባል ተደረገላቸው፡፡

በሚቀጥለው ቀን ዲኖና ሲሳይ የአዳኞቹን ጆንያ በአቅራቢያቸው ወዳለው የጫካው ጥበቃ ጣቢያ በመውሰድ አስረከቡ፡፡

“ጥሩ ሥራ ነው የሰራችሁት! እንደ አናንተ ያሉ ትናንሽ የጫካ ጠባቂዎች በጣም ይጠቅሙናል” በማለት የጠባቂዎቹ ኃላፊ እነ ዲኖን አመሰገናቸው፡፡



# ስግብግቡ ጂብና ብልጧ አህያ

## ከዜናማርቆስ እንዳለው

አንድ ጊዜ አንድ ጅብና አህዩት መንገድ ላይ ተገናኙ፡፡

“እንደምን ዋልሽ?” አለ ጅብ፡፡

“እግዚአብሔር ይመስገን!” አለች አህዩት፡፡

“ወዴት እየሄድሽ ነው?” አለ ጅብ፡፡

“ውሃ ልጠጣ ወደ ወንዝ እየወረድኩ ነው” አለች፡፡

“እንዴት ያለ ገጠመኝ ነው? እኔም እኮ እንዳንቺው ውሃ ልጠጣ ወደ ወንዝ እየወረድኩ ነው፡፡ በይ አብረን እንሂድ!” አለና ጅቡ ሳቀ፡፡



ምሳ ሰዓት ነበር፡፡ እያወሩ ጎን ለጎን መሄድ ጀመሩ፡፡ ቀኑ በጣም ሞቃታማ ስለነበር ደክሟቸውም ስለነበር ከአንድ ዛፍ ጥላ ስር አረፍ አሉ፡፡

“ለመሆኑ አንቺ የምትኖሪበት ቦታ አንችን የመሳሰሉ ብዙ ቆንጆዎች አሉ?” አላት ጅብ እያጋነነ በማድነቅ፡፡

“እግዚአብሔር ከአይን ይሰውረን እንጂ ብዙ ነን፡፡ ሁሉም ታዲያ ሲበዛ ቆንጆዎች ናቸው፡፡” ጅቡ የፈለገው ዘሎ አህያዋን መዘንጠል ብቻ ነበር፡፡

“በሰፈራችሁ ጨርሶ ውሃ የለም?” ሲል ጠየቃት፡፡

“የለም በክረምት ብዙ ውሃ እናገኛለን፡፡ ምንጮቹም በየቦታው ይፈልቃሉ፡፡ ቀድተን ሁሉ ወደ ቤታችን እንወስዳለን፡፡ አሁን ግን በበጋ ምንጮቻችን ባዶ ናቸው፡፡ ስለዚህ ጥማችንን ለማርካት ወደ ወንዙ እንወርዳለን፡፡ በአንተ ሰፈርስ



እንዴት ነው? ምንም ውሃ የለም?” አለችው፡፡

“በፍፁም! እኔ በምኖርበት ቁጥቋጦ ወንዝም ሆነ ምንጭ የለም” አላት፡፡

“ታዲያ ለምን ውሃ ወዳለበት ሠፈር አትሄድም?”

“ስለለመድኩት ነው፡፡ ከለመዱት እኮ መቃብርም ይሞቃል” አላት ተንከትክቶ እየሳቀ፡፡

“እስከዚህ ሞኝ አትሁን፤ እስካለህ ድረስ ሕይወትህን መጠበቅ አለብህ!” አለችው፡፡

“በይ ብዙ አረፍን፤ ጉዟችንን እንቀጥል” አለ ጅቡ ቆሞ እየተወጣጠረ፡፡

“በይ ሂጂ ቅደሚ!” አላት፡፡

“እኛ ሀገር ወንድ ነው ከፊት የሚሄደው፡፡ ምክንያቱም መንገዱን የሚውቀው እሱ ስለሆነ ይመራናል፡፡ ስለዚህ አንተ ቅደም!” አለችው፡፡

“በእኛ ሀገር ደግሞ ተቃራኒው ነው” አላት ከፊት ለፊቷ እየሄደ፡፡ “ሴቶች ይቀድማሉ፤ ወንዶች ይከተላሉ፡፡ በዚህ አይነት በሴቷ ላይ አደጋ ቢደርስ ወንዱ ወዲያው ከአደጋ ሊያድናት ይችላል” በማለት እያስረዳት ከፊት እንድትቀድም ይገፋፋታል፡፡ ይሁን እንጂ አህዩት በተደጋጋሚ ከኋላ ሆና መሄድ እንደምትፈልግ ትነግረዋለች፡፡ የሆነ ሰዓት ላይ የጅቡ ፀባይ እያስፈራት መጣ፡፡ አድብቶ መጥፎ ነገር ሊፈፅም ነው ስትል አሰበች፡፡

ጅቡ ወሬውን በመቀጠል ከፊት ቀድማ እንድትሄድ ሊያሳምናት ቢሞክርም አህዩት ግን ለማምለጥ ወሰነች፡፡ ከዚያም ዞረችና ፈረጠጠች፡፡



“እባክሽ ነዒና ከፊት ቅደሚ!” አለ ጅቡ ትእግስቱ እያለቀና ከመጎምዠቱ የተነሳ ምራቁን እየዋጠ፡፡ ምንም መልስ ሲያጣ ጊዜ ዞር ቢል በሩቁ የአቧራ ደመና ታየው፡፡



# ድንቡሼና ጓደኞቹ

## ከሜሪ ጃፋር

ድንቡሼ የስድስት ዓመት ልጅ ነው፡፡ የተወለደው ስድስት ኪሎ አካባቢ ሰባ ደረጃ በሚባል ሠፈር ነው፡፡ እዚህ ሠፈር ድንቡሼን የሚያካክሉ ብዙ ልጆች አሉ፡፡ ድንቡሼ ብዙ ጓደኞች አሉት፡፡ ጓደኞሞቹ ሌባና ፖሊስ፤ ድብብቆሽ፤ አባሮሽ፤ ሰኞ ማክሰኞ፤ ብይ፤ እግር ኳስ ይጫወታሉ፡፡ ኳስ በሚጫወቱበት ጊዜ ድንቡሼ ብዙ ጎል ስለሚያገባ ጓደኞቹ ያደንቁታል፡፡

አንድ ቀን ድንቡሼ ከጨዋታ ወደ ቤቱ ሲመለስ አባትና እናቱ የቤታቸውን እቃዎች፤ ምንጣፍ እና በእቃዎች የተሞላ ካርቶን በመልክ በመልክ እያደረጉ ይደረድራሉ፡፡ ጎረቤቶቻቸውም ያግዟቸዋል፡፡ ድንቡሼ ምን እየተደረገ እንደሆነ አልገባውም፡፡

”ለምንድነው እቃዎች ሁሉ የምትጠርዙት” ሲል አባቱን ጠየቀ፡፡

“ሌላ ቤት ልንገባ ነው፡፡”

“ከዚህ ሠፈር ለቀን”

“አዎ! ከዚህ ለቀን ሌላ ሠፈር እንገባልን!” አሉ አባቱ

“አዲሱ ቤታችን ነው”

“አዎን! ከአሁን በኋላ የምንኖርበት ሠፈር ኮተቤ ነው የሚባልው”

“ኮተቤ ሩቅ ነው”›

“አዎን! ከዚህ በጣም ይርቃል”

“ታዲያ. . . እኔ እዚያ ከማን ጋር . . . እጫወታልሁ”

“ከዚያው የሠፈር ልጆች ጋር”

“እዚያም የሠፈር ልጆች አሉ”

“በሚገባ!” አባትየው ሳቁ “ልክ እንደዚህ ሠፈር ብዙ ልጆች አሉ፡፡”

ድንቡሼ አንድ ጥግ ቁጭ ብሎ ትላልቆቹ ሰዎች እቃዎቹን ከቤት እያወጡ ጉብታው ላይ ሲያስቀምጡ ይመለከታል፡፡ ጭንቅ ብሎታል፡፡ “ምናልባት ኮትቤ ያሉት ልጆች ጥሩዎች ላይሆኑ ይችላሉ፤ ምናልባትም ላይወዱኝ ይችላሉ፤ እኔ ደግሞ እዚህ ከጓደኞቼ ጋር መሆን ነው የምፈልገው . . .” ሲል አሰበ፡፡ ግን ይህን ሃሳቡን ለማንም አልተናገረም፡፡ የእቃ መጫኛው መኪና መጣ፡፡ የሠፈሩ ሰዎች እቃውን በመጫን አገዟቸው፡፡ ጭነው፤ ጨርሰው ጎረቤቶቹ ከድንቡሼ ቤተሰቦች እና ከድንቡሼ ሲሰናበቱ ብዙዎቹ አለቀሱ፡፡ ድንቡሼ እና ጓደኞቹም ተላቀሱ፡፡





ወደ ኮተቤ የሚወስደው መንገድ ረጅም ነው፡፡ በዚህ ላይ መንገዱ ላይ ብዙ መኪኖች አሉ፡፡ ድንቡሼ እናቱ አጠገብ ተቀምጧል፡፡ በጣም አዝኗል፡፡ እናቱ ላይ ደገፍ ብሎ ከጓደኞቹ ጋር ስለነበረው ስንብት ያስባል፡፡ ሲሰናበታቸው እያቀፉ ይስሙት ነበር፡፡ ጎል ባገባ ቁጥር እንዴት ያደንቁት እንደነበር ትዝ አለው፡፡

ድንገት መኪናው ሲቆም ከሐሳቡ ብንን አለ፡፡ ሁሉም ከመኪናው ወረዱ፡፡ ትላልቆቹ እቃውን ማውረድ ጀመሩ፡፡ አዳዲሶቹ ጎረቤቶችም ያግዟቸው ጀመር፡፡

ድንቡሼ ድንገት የልጆች ድምፅ ሰማ፡፡ በአቅራቢያው ባለው ሜዳ ላይ ልጆች ኳስ ይጫወታሉ፡፡ በጣም የሚያምር እና ትልቅ የኳስ ሜዳ ነው፡፡ ድንቡሼ ደስ አለው፡፡ ወደ ልጆቹ ሄዶ መጫወት ፈለገ፡፡ ግን ድፍረት አጣ፡፡

“ሂድ ከልጆቹ ጋር ተጫወት!” ሲሉ አባቱ አደፋፈሩት፡፡

ድንቡሼ ጥቂት እርምጃ ወደ ሜዳው ተጠጋና ቆመ፡፡

“ና! ከእኛ ጋር ተጫወት!” አለው አንዱ ልጅ፡፡ ልጁ በግምት እኩያው ቢሆን ነው

ድንቡሼ ከልጁ ጋር ወደ ሜዳው ገባ፡፡ አንድ ሌላ ልጅ ኳሱን አቀበለው፡፡ ድንቡሼ ተቀብሎ ለሌላ ልጅ አቀበለ፡፡ ድንቡሼ በአዲሱ ሠፈር፤ ኮተቤ፤ ኳስ እየተጫወተ ነው፡፡





# የጉንዳኖቹ አገር

ከይኼነው ወርቁ

ትምህርት ቤት ተዘግቷል፡፡ ቡጡን፣ ሚሚንና አቡሽን ውጭ አገኘኋቸውና ኩኩሉ ለመጫወት ተስማማን፡፡ ብዙ ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎች እና ቋጥኞች ወዳሉበት ቦታ ሄድን፡፡ በመጀመሪያ ቆጣሪ እንዲሆን የተመረጠው ቡጡ ነበር፡፡ እስከ መቶ ድረስ እየቆጠረ እያለ ለመደበቅ ተበታተንን፡፡

ሚሚ እና አቡሽ ከዛፎቹ ኋላ ሲደበቁ እኔ የተሻለ ቦታ መፈለግ ጀመርኩኝ፡፡ ከረዣዥሞቹ ዛፎች መካከል አንድ ትልቅ ጉቶ አለ፡፡ የጉቶውን እዚያ ቦታ መኖር የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ፡፡

„ከጉቶው ኋላ ብደበቅ ማንም አያየኝም፣ ከዚህ የተሻለ መደበቂያ ቦታ አይኖርም“ ስል አሰብኩኝ፡፡ ቡጡ እስከ መቶ ድረስ ቆጥሮ በመጨረስ እኛን በመፈለግ ላይ ነው፡፡

ድንገት በመቶዎች በሚቆጠሩ መርፌዎች የተወጋሁ ይመስል ሰውነቴ ላይ የሆነ የሚቆጠቁጥ  ስሜት ተሰማኝ፡፡ በጣም ጮኼ ከተደበቅኩበት ቦታ ዘልዬ ወጣሁ፡፡

„አይቼሃለሁ! አንደኛ! አንደኛ!„ አለ ቡጡ በደስታ እየሮጠ፡፡

እኔ ግን „ወይኔ! ወይኔ!„ እያልኩ እየጮኹኩ ነው፡፡ ጆሮዬ ላይ፣ አንገቴ ላይ፣ አይኔ ላይ፣ ጀርባዬ ላይ፣ እግሬ ላይ፣ የእግሬ አውራ ጣት ላይ፣ ሰውነቴ ላይ ሁሉ የሚርመሰመስ ነገር አለ፡፡

„ዋይ!„ እያልኩ በድጋሚ በመጮህ እንደ አውሬ እዘላለሁ፡፡

„ወይኔ! ጉንዳኖች ናቸው!„ አልኩኝ፡፡ በተናካሾቹ ትናንሽ እንሰሳት ተወርሮ ጥቁር ወደ ሆነው ጉቶ እያመለከትኳቸው፡፡ ሚሚና አቡሽ ከተደበቁበት ወጥተው መጡ፡፡ ሸሚዜንና ሱሪዬን አወለቅኩኝ፡፡ ከልብሶቹ ላይ ሁሉንም ጉንዳኖች አራግፈን ቸርሰን ልብሱን እንደገና እስክለብስ ድረስ ጥቂት ጊዜ ወሰደብኝ፡፡





የዚህን እለት ኩኩሉ መጫወታችንን ትተን ወዲያና ወዲህ እየተጣደፉ በስራ የተጠመዱ የሚመስሉትን ጉንዳኖች መመልከት ቀጠልን፡፡



„ከመደበቄ በፊት ቦታውን በደንብ ማየት ነበረብኝ!„ አልኩኝ ለጓደኞቼ፡፡

„ልክ ነህ! ጉንዳኖቹ ስራ እየሰሩ ባለበት ሰዓት ነው የረበሽካቸው፡፡„

„እሱ ብቻ አይደለም፡፡ እነዚህ ጉንዳኖች ‚ወታደሮች‘ ይባላሉ፡፡„ አለ አቡሽ እጅብ ወዳሉት ትላልቅ ጉንዳኖች እያመለከተን፡፡

„ሲወሩህ አገራቸውን ከጠላት መከላከላቸው ነበራ!„ አለች ሚሚ፡፡

„በሉ እሺ እኔ ከጉንዳኖች ጋር ጦርነት መግጠም አልፈልግም፡፡ ወደ ሌላ ቦታ እንሂድና ሌላ ጨዋታ እንጫወት፡፡„ አልኩኝ እየሳቅኩ፡፡



# ዷንሺ ሳሮን ዷንሺ

## ከአስቴር በዳኔ

ሳሮን የስምንት ዓመት ልጅ ስትሆን የፎንታኒና ትምህርት ቤት ተማሪ ነች፡፡ በየዓመቱ የወላጆች በዓል ሲከበር በተማሪዎች የሚዘጋጅ የሙዚቃ ሥነ-ጽሑፍ ንባብና ድራማ ይቀርባል፡፡ ለዚህ ተብሎ ታዲያ የተለያዩ ክበቦች ይቋቋማሉ፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ አንዱ ክበብ ውስጥ በመመዝገብ ተሳትፎ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ሳሮን ብዙ ጊዜ ብቸኛ ነች፡፡ ጓደኞች የሏትም፡፡ ከማንም ጋር አትጫወትም፡፡ ክፍል ውስጥ የምትቀመጠው ከኋላ ነው፡፡ አንዱም ክበብ ውስጥ አልተመዘገበችም፡፡

„ሳሮን ጌታቸው! ወዲህ ነይ!„ ስትል መምህሯ መምህርት እጅጋየሁ ቁጣ በተሞላበት ድምፅ ጠራቻት፡፡ ሳሮን ፈራች፡፡

„ለምንድን ነው አንዱ ክበብ ውስጥ ያልተመዘገብሽው?„

ሳሮን ምን መመለስ እንዳለባት ግራ ገብቷት መሬት መሬት ትመለከት ጀመር፡፡

„እሺ! አንዱ ክበብ ውስጥ መግባት ካልቻልሽ እኔ እመድብሻለሁ፡፡ ለወላጆች ቀን ትደንሻለሽ„ አለቻት መምህርት እጅጋየሁ ምንም መልስ ሳትጠብቅ፡፡

„እኔ እኮ መደነስ አልችልም!„ አለች ሳሮን፡፡ አይኗ እምባ እያቀረረ፡፡

„አድምጪ! አልችልም አይባልም፣ እሞክራለሁ ነው የሚባለው፡፡ ከዛሬ ጀምሮ መለማመድ ጀምሪ፡፡ አሁን ወደ ቦታሽ ተመለሺ„

ሳሮን ከትምህርት ቤት መልስ ወደ ቤት እንደመጣች የሆነ የተፈጠረ ነገር መሆኑን እናቷ ያወቀችው ወዲያው ነበር፡፡ „ምን ሆነሻል? ለምንድን ነው ለንቦጭሽን የጣልሽው?„ አለቻት፡፡

„መምህሬ ለወላጆች ቀን ዳንስ የሚያቀርቡ ልጆች ቡድን ውስጥ መዘገበችኝ?„

„ለምንድን ነው የምትደንሺው? ትምህርት ቤት የምትሄጂው እኮ ልትማሪ እንጂ ልትደንሺ አይደለም!„ በማለት እናቷ በቁጣ ተናገረች፡፡

„እሺ! ነገ ለመምህሬ እንደሱ ብዬ እነግራታለሁ„ አለች ሳሮን በደስታ፡፡

በነጋታው መምህሯ በድጋሚ ሳሮንን ጠራቻትና፣ „እሺ ዳንሱን ተለማመድሽ?„ አለቻት፡፡

„አልተለማመድኩም፡፡ እናቴ ... እንዳለች... እኔ ... ትምህርት... ትምህርት ቤት ... የምሄደው ለመማር እንጂ፣ እንዴት እንደሚደነስ ... „ ብላ ተናግራ ሳትጨርስ፣

„አሃ ይህ ማለት ችግሩ ያለው እናትሽ ጋር ነው ማለት ነው„ በማለት ኮስተር ብላ ተናገረችና ቴፑን ከፈተችው፡፡ ሙዚቃው ሲጀምር ሌሎቹ ተማሪዎች ክብ



ሰርተው እንዲቀመጡ አዘዘቻቸውና „በይ ሳሮን ተማሪዎቹ ፊት ደንሺ!„ ስትል አዘዘቻት፡፡

ሳሮን አልተንቀሳቀሰችም፡፡ ልታለቅስ ትንሽ ቀራት፡፡

„ሳሮን ደንሺ!„ መምህሯ ጮኽ ብላ ተናገረች፡፡ ሁሉም አፍጥጠው ይመለከቷታል፡፡

„ሳሮን ደንሺ!„ አሁንም የመምህሯ ድምፅ በጣም ጮኽ ብሎ ነበር፡፡



ሳሮን ሽምቅቅ አለች፡፡ ሌሎቹ ተማሪዎች ሳቁባት፡፡

„ሳሮን ደንሺ!„ ሁሉም ተማሪዎች በአንድ ላይ ተናገሩ፡፡

ሳሮን ከዚህ በላይ መታገስ አልቻለችም፡፡ ዞረችና ከክፍሉ ሮጣ ወጣች፡፡ የኮሪደሩ መጨረሻ እስክትደርስ ድረስ ሮጠች፡፡ እዚያ እንደደረሰች ግድግዳውን ተደግፋ ማልቀስ ጀመረች፡፡

„ምን ሆንሽ?„ አላት የሙዚቃ መምህሩ የመምህር ኤሊያስ ድምጽ፡፡

„ምንም!„ አለች እየተንሰቀሰቀች፡፡

„አይዞሽ ሳሮን ምናልባት እኔ የምረዳሽ ነገር ካለ ንገሪኝ!„ አላት፡፡ በዚህን ጊዜ ሳሮን ሁሉንም ነገር ነገረችው፡፡

„መደነስ እንደማልችል ለመምህሬ ነግሬያት ነበር፡፡ ይባስ ብላ ከተማሪዎቹ ፊት ወጥተሽ ደንሺ አለችኝ ... እነሱ ደሞ ሳቁብኝ... „ መምህር ኤልያስ አዘነ፡፡

„አንድ ሃሳብ አለኝ፡፡ ዳንስ መማር ትፈልጊያለሽ?„ ሳሮን በመስማማት አንገቷን ነቀነቀች፡፡

„ምንም ችግር የለም እኔ አስተምርሻለሁ!„

ከዚያን ቀን ጀምሮ የሙዚቃ መምህሩ ኤልያስ በየቀኑ ለአንድ ሰዓት ዳንስ ያስተምራት ጀመር፡፡ የዳንስ ፊልም ከፍቶ ሲያሳያት ሁሉም መጀመሪያ እንደሷ ሲሳታቱ ተመለከተች፡፡ „ለካ እኔ ብቻ አይደለሁም የምሳሳተው„ አለችው፡፡

„ማንም ጎበዝ ሆኖ አልተወለደም፡፡ ልምምድ ደግሞ ጎበዝ ያደርጋል፡፡ ተስፋ አትቁረጪ!„ እያለ ያበረታታል፡፡

„እንዳልሳሳት እፈራለሁ„ አለች ሳሮን አቀርቅራ፡፡

„ክፍል ውስጥ እንኳን ጥያቄ ሲጠየቅ መልስ ለመስጠት አልደፍርም... „

„ስህተት እሰራለሁ ብለሽ እንዳትፈሪ፡፡ ሰው ሁሉ ይሳሳታል፡፡ ትላልቅ ሰዎች ሁሉ ይሳሳታሉ፡፡ ዋናው ነገር ከስህተትሽ መማርሽ ነው„ በማለት መምህር ኤልያስ አደፋፈራት፡፡

ለወላጆች ቀን የተለያዩ ዝግጅቶች ነበሩ፡፡ ሁሉም ዝግጅቱን ለማቅረብ በጉጉት ይጠብቃል፡፡ ሳሮንም እንዲሁ፡፡ ባለፉት ሳምንታት በትጋት ስትለማመድ ነበር፡፡ የሙዚቃ መምህሩም በእርሷ በጣም ደስተኛ ነው፡፡ እሷም ለመደነስ ምንም ፍርሃት አይሰማትም፡፡ ክፍል ውስጥ ሁሉ እንደበፊቱ በጣም አትፈራም፡፡ ተራዋ ደርሶ መድረኩ ላይ ስትወጣ ልቧ ትንሽ ትንሽ ይመታ ነበር፡፡ የሙዚቃ መምህሩን አየችው፡፡ ፈገግ ብሎ አንገቱን ነቀነቀላት፡፡ የክፍል ጓደኞቿ በሳሮን ዳንስ ለመሳቅ ተዘጋጁ፡፡

ሙዚቃው እንደተጀመረ ሳሮን መምህር ኤልያስ እንደነገራት አደረገች፡፡ የተሰበሰበውን ሰው ረስታ ሙዚቃውን ተከትላ ፊቷ ላይ ፈገግታ እየተነበበ፣ የተለማመደችውን ዳንስ ማቅረብ ጀመረች፡፡ ሁሉም ተገርመው አደናነሷን አደነቁ፡፡

„የኔ ልጅ ናት!„ በማለት እናቷ አብረዋት ለተቀመጡ ሁለት ሴቶች በኩራት



ተናገረች፡፡

ሙዚቃው አብቅቶ ሳሮን ከህዝቡ ፊት ጎንበስ ብላ ስትሰናበት ሁሉም በከፍተኛ አድናቆት አጨበጨቡ፡፡ ሳሮን ከመምህርት እጅጋየሁ አጠገብ ወደ ቆመው መምህር ኤሊያስ ሮጠች፡፡

„አመሰግናለሁ!„ አለችው በደስታ እያየችው፡፡ መምህርት እጅጋየሁ ግራ በተጋባ ሁኔታ ተመለከተቻት፡፡



„እንዴት ነው በእዚህ ፍጥነት ቆንጆ ዳንስ መደነስ የቻልሽው?„ አለቻት፡፡

„መምህር ኤልያስ አሰለጠነኝ„ አለች ሳሮን፡፡

„አዎን ! እኔ እረድቻት ነው፡፡ መጀመሪያ ላይ ሳሮን ትፈራ ነበር… ቀስ በቀስ ግን ይበልጥ በራሷ እየተማመነች መጣች…„

„እንኳን ነገርከኝ … አመሰግናለሁ ኤልያስ„ አለችው፡፡ መምህርት እጅጋየሁ ጥፋቷ ገብቷታል፡፡ ወደ ሳሮን ዞር ብላም „በሌላ ጊዜ የሆነ አዲስ ነገር መማር ከፈለግሽ እኔ አግዝሻለሁ እሺ!„ አለቻት፡፡



# ቦቢ የት ነህ?

ከዮናስ ሞገስ

መአዛ ከእናቷ፣ ከአባቷ፣ ከቦቢ እና ውሮ ጋር አዲስ አበባ ውስጥ ትኖራለች፡፡ ቦቢ የውሻዋ ስም ሲሆን ውሮ ደግሞ የድመቷ ስም ነው፡፡

መአዛ ቦቢና ውሮን ትወዳቸዋለች፡፡

መአዛ የሚያምር ኳስ አላት፡፡ ኳሱን ይዛ ወደ አትክልት ስፍራ በመሄድ „ቦቢ! ውሮ! ኑ እንጫወት!„ ብላ ትጠራቸዋለች፡፡ ሁለቱም እየሮጡ ይመጣሉ፡፡

መአዛ ኳሱን ለቦቢ ትወረውርለታለች፡፡ ቦቢም ኳሱን ይይዝና ለመአዛ ያመጣላታል፡፡ ለውሮ ደግሞ ትወረውርለታለች፡፡ ውሮ ኳሱን እያንከባለለች ትጫወታለች፡፡



„እማዬ፣ ቦቢና ውሮ እንዴት በኳሱ እንደሚጫወቱ ተመልከች!„ ትላለች መአዛ፡፡

„በጣም ደስ ይላሉ!„ በማለት እናቷ ደስታዋን ትገልፃለች፡፡

ከጨዋታ በኋላ መአዛ የቦቢን ፀጉር ስታበጥርለት ቦቢ ደስ ይለዋል፡፡

ድመቷን ስታሻሽት ተመችቷት የደስታ ድምፅ ታሰማለች፡፡ ውሮ ስትዳበስ ደስ ይላታል፡፡

አንድ ቀን ጠዋት በኳሱ ሲጫወቱ ኳሱ አጥሩን አልፎ ወደ ውጪ ወጣ፡፡ መአዛ ከቦቢና ውሮ ጋር ሆኖ ወደ ውጭ በመውጣት ኳሱን ፈለጉ፡፡ ሊያገኙት ግን አልቻሉም፡፡ እያዘኑ ባዷቸውን ወደ አትክልቱ ስፍራ ተመለሱ፡፡

ትንሽ ቆይቶ ቦቢ ጠፋ፡፡ መአዛ ሁሉ ቦታ ፈለገችው፡፡



„ቦቢ የት ነው ያለኸው?„ እያለች መአዛ በተደጋጋሚ ተጣራች፡፡

„ውሮ፣ ቦቢ የት ነው?„ በማለትም ጠየቀቻት፡፡

„ሚያው!„ በማለት ውሮ በሃዘን መለሰችላት፡፡

„እማዬ! አባዬ! ቦቢ ጠፋ!„ አለች መአዛ እያለቀሰች፡፡

„አይዞሽ የትም አይጠፋም! እኛ እናፋልግሻለን„ አለቻት እናቷ፡፡

መአዛ፣ እናቷ፣ አባቷ እና ውሮ ቦቢን ሲፈልጉት ዋሉ፡፡ ግን በፍፁም ሊያገኙት አልቻሉም፡፡ መምሸት ሲጀምር ቦቢ ተመልሶ መጣ፡፡ በአፉ የሚያምረውን ኳስ ይዟል፡፡



መአዛ፣ እናቷ፣ አባቷ እና ውሮ ተደሰቱ፡፡ ቦቢም ተመልሶ ወደ ቤቱ በመምጣቱ ብቻ ሳይሆን ኳሱንም ስላገኘው ተደስቷል፡፡ ዘሎ መአዛ እቅፍ ውስጥ ገባ፡፡

„ቦቢ ኳሱን ልትፈልግ ሄደህ ነው የጠፋኸው?„ስትል መአዛ ጠየቀችው፡፡

„ዋው! ዋው!„ በማለት ቦቢ ጮኸ፡፡

# ሊስትሮው አብዲ

ከገበየሁ አየለ

አብዲ የሊስትሮ እቃውን እንደያዘ አንድ ግንብ ስር ተቀምጧል።



ከጠዋት ጀምሮ ጫማ የሚያስጠርጉ ሰዎች እየጠየቀ እስከ አምስት ሰአት ድረስ ያገኘው ዘጠኝ ብር ብቻ ነው። ከሰአት በኋላ ይማራል።

ዛሬ ሃሳቡ ሁሉ ስለ እናቱ ነው። እናቱ ታመዋል። ትላንትና ሐኪም ቤት ወስዷቸው ነበር፡፡ ለምርመራ የሚበቃ ገንዘብ የነበራቸው ቢሆንም፣ለታዘዘላቸው መድሃኒት መግዣ የሚሆን በቂ ገንዘብ ግን አልነበራቸውም።

„ዛሬ ከትምህርት ቤት ቀርቼ ቀኑን ሙሉ ስሠራ ብውል ይሻላል። ምናልባት ለእናቴ ለመድሃኒት መግዣ በቂ ገንዘብ አገኝ ይሆናል…“ በማለት አሰበ።

አሁንም ስለ እናቱ መጨነቁ አልቀረም። ጠዋት ተሰናብቷቸው ከቤት ሲወጣ ትኩሳታቸው በጣም ከፍ ብሎ ነበር። ‹ብሶባት ቢሆንስ?› በድንገት አብዲ ፍርሃት ወረረው። የሊስትሮ ሳጥኑን ያዘና በሩጫ ወደ ቤቱ ሄደ።



እናቱ ትቷቸው እንደሄደ አልጋ ላይ ተኝተዋል። ፊታቸው ገርጥቷል፤ላብ በላብ ሆነዋል፤ ያቃስታሉ።

„እማዬ እንዴት ነሽ?“ አለ በሹክሹክታ።

„አሁን ይሻለኛል!“

„ግን እኮ ታተኩሻለሽ…“ አለ ፊታቸውን እያሻሸ። እንባ ተናነቀው።

„አይዞህ አታስብ፤ ማድቤት ውስጥ ከትላንት የተረፈ ምግብ አለልህ። እሱን ብላና ቶሎ ወደ ትምህርት ቤት ሂድ። ማርፈድ የለብህም!“ አሉት እያቃሰቱ።

„ዛሬ ዘጠኝ ብር አግኝቻለው፤ምናልባት በዚህ ግማሹን መድሃኒት መግዛት እችል ይሆናል“ አለ ማልቀሱን እንዳይታወቅበት እየሞከረ።

„የሚበቃ አይመስለኝም፤አብዲ አታልቅስ እንጂ፤ አሁን ደህና እሆናለው“ አሉ እናቱ ሊያፅናኑት እየሞከሩ።

አብዲ ዘጠኝ ብሩን ይዞ ወደ ውጭ እሮጠ። ብዙ መንገዶችን አቋርጦ አረንጓዴ የውጭ በር ያለው ግቢ አጠገብ ሲደርስ ቆመ። ግቢው ውስጥ አንድ ሐኪም ከነቤተሰቡ ይኖራል። አብዲ ለሰዎቹ ብዙ ጊዜ ጫማቸውን ጠርጎላቸው ያውቃል። በዚህ ምክንያት ቤተሰቡ ይወደዋል።

አብዲ ቆም ብሎ ትንሽ አሰበና በሩን አንኳኳ። አንዲት እኩያው የምትሆን ልጅ ከፈተችለት።

„አባትሽ አሉ?“ አለ እየተጨነቀ።

„አለ፤ ግባ!“ አለችና አባቷ ወደ አሉበት ስፍራ ወሰደችው።

አብዲ እንባውን እየጠራረገ ስለታመሙት እናቱ ለዶክተሩ እንዲህ እያለ ነገረው፤ „እናቴ በጣም ታማብኛለች። መድሃኒት መግዣ በቂ ገንዘብ የለኝም። እባክዎ ዶክተር ይርዱኝ። ወደፊት ሰርቼ እከፍልዎታለሁ!“

„ስለ ክፍያው በኋላ እንነጋገራለን። አሁን ለእናትህ እርዳታ ማድረግ እንድችል ወደ ቤት እንሂድ!“ አለ ሐኪሙ ፈገግ ብሎ።

ሐኪሙ የህክምና እቃዎቹን ያዘና አብዲን ተከትሎ ወደ ቤታቸው ሄደ። የአብዲ እናት የመጣውን ሰው ከዚህ በፊት አይተውት ስለማያውቁ ትንሽ ፈሩ። እሱ ግን መርምሮ የሚዋጥ መድሃኒት ሰጣቸውና፣ „አይዞህ አብዲ፤ የማስታገሻ መድሃኒት ስለወሰዱ እናትህ ቶሎ ይሻላቸዋል“ አለ።



„ትላንት የታዘዘላት መድሃኒት ይሄ ነበር" በማለት አብዲ የትእዛዝ ወረቀቱን ለሐኪሙ አሳየው። እሱም ትእዛዙን ካነበበ በኋላ፤

„መድሃኒቱ ለእናትህ ያስፈልጋቸዋል"

„ገንዘቡ የለንም እንጂ እሱስ ..." አሉ የአብዲ እናት እያቃሰቱ።

„እኔ እሰጣችኋላሁ!" አለ ዶክተሩ የገንዘብ ቦርሳውን ከኪሱ እያወጣ ።

„አመሰግናለው! በተቻለኝ አቅም ገንዘቡን ቶሎ እመልስልዎታለው። ጫማ ጠርጌ የመድሃኒቱን ዋጋ እስክከፍል ትምህርት ቤት አልሄድም!" አለ አብዲ በደስታ።

„ገንዘቡን መመለስ አያስፈልጋችሁም። ትምህርትህን ማቋረጥ የለብህም። ጥሩ ልጅ ስለሆንክ አንተንም ሆነ እናትህን መርዳት ደስ ይለኛል!" አለ ሐኪሙ እጁን አብዲ ትከሻ ላይ አሳርፎ። አብዲ የሆነ ነገር ከኪሱ አወጣና እጁን ወደ ሐኪሙ ዘረጋ ።

„ምንድነው እሱ? „ አለ ሐኪሙ እየተገረመ።

„ዛሬ ሰርቼ ያገኘሁት ዘጠኝ ብር ነው... ለመድሃኒት መግዣ የሚሰጡን ብር ላይ ይጨምሩት..."

„አያስፈልግም አብዲ፤ መድሃኒቱን እኔ እገዛለው አልኩ እኮ" አለ እየሳቀ።

„አያውቁንም ግን እርዳታ አደረጉልን ... አላህ ይስጥዎት! „ አሉ የአብዲ



እናት ሐኪሙን እየተመለከቱ።

„ችግረኛ በሽተኞችን መርዳት ሰብአዊ ግዴታዬ ነው። ነገ መጥቼ እይዎታለሁ!" ካለ በኋላ ወደ አብዲ ዞር ብሎ፤" አብዲ! አንተ ደግሞ ሁሌም ከእኔ የምትፈልጉት እርዳታ ሲኖር መጥተህ ንገረኝ" አለው።

አብዲ ከሐኪሙ ጋር ሄዶ መድሃኒቱን ገዝቶ መጣ። እናቱ መድሃኒቱን ከወሰዱ በኋላ ወዲያው ተሻላቸው።

አሁን አብዲ ጫማ አይጠርግም። በዚያ ፈንታ የዶክተሩን ልጆች ያስጠናል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሆኗል።

„ትምህርቴን እስከ ዶክተርነት ተከታትዬ እንደትልቁ ጓደኛዬ ጥሩ ዶክተር በመሆን ችግረኛ በሽተኞችን አክማቸዋለሁ!" በማለት ላይ ነው።

# መልካሙ ቁራ

ከታምሩ ለገሰ

በአባቴ አሮጌ ካልሲ የሰራሁትን ምርጥ ኳስ ከግድግዳው ጋር እያጋጨሁ እየተጫወትኩ ነው፡፡ ግድግዳው የኔ ተጋጣሚ ነው፡፡

„ኸረ ተው ግድግዳውን ታፈርሳለህ!„ አለችኝ እናቴ በበሩ ብቅ ብላ፡፡

አንድ ጊዜ እንደገና ኳሱን ከግድግዳው ጋር አጋጨሁ፡፡

„ኸረ ተው አንተ ልጅ! ተው! ካለዚያ ኳሱን ነው የምቀማህ!„ አለችኝ በድጋሚ በጣም ተቆጥታ፡፡

„እሺ እተዋለሁ!„ ብዬ አጉረመረምኩ፡፡

ኳሱን ከግድግዳ ጋር ማጋጨቱን ትቼ ወደ ላይ እየወረወርኩ መቅለብና መጫወት ጀመርኩ፡፡ ግን ወዲያው ሰለቸኝና ዞር ዞር ብዬ ስመለከት አሪፍ አጫዋች አገኘሁ፡፡ የቤታችን ጣራ፡፡

ኳሱን ጣራ ላይ እየወረወርኩ ተንከባሎ ሲመጣ ልክ እንደ በረኛ ቀለብኩ፡፡ ልክ እንደ ተከላካይ ወደ ጣራው ጠለዝኩት፡፡ ተንከባሎ ሲመጣ ቀለብኩት፡፡ ‚ደስ ሲል‘ አሁን ደግሞ ልክ እንደ አጥቂ ተጫዋች ሆኜ መታሁት፡፡ ወይኔ! ተመልሶ አልወረደም፡፡ ኳሱ ጣራው ላይ ቀረ፡፡

„ይሄን ልጅ ምን ባደርገው ይሻለኛል እባካችሁ! ለምንድን ነው የምነግርህን የማትሰማው? አምጣ ወዲህ ኳሱን! የታል?„ አለችኝ እናቴ በረንዳው ላይ ቆማ፡፡ በጣም ተቆጥታለች፡፡

„ጣራው ላይ ተሰቀለብኝ ... እማ ...„ ተንተባተብኩ፡፡

„ጎሽ! ግልግል፡፡ እኛም ሰላም እናገኛለን„ አለችኝ ጭንቅላቷን እየነቀነቀች፡፡

መጥረጊያችንን አመጣሁና ኳሱን ከጣራው ላይ ለማውረድ ሞከርኩኝ፡፡ አልደርስ አለኝ፡፡ እንዲረዝምልኝ በማሰብ ሌላ እንጨት መጥረጊያው ላይ ቀጠልኩበትና በእሱ ለማውረድ ሞከርኩኝ፡፡ ግን ኳሱ አጠገብ እንኳን ሊደርስልኝ አልቻለም፡፡ በነጋታው ኳሴ እንዴት እንዳደረ ለማየት በጠዋት ከቤት ወጣሁ፡፡ እዚያው ጣራው ላይ እንዳለ ነው፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዴ በፊት በምልክት ተሰናበትኩት፡፡

„ኳስህን ለምን አላመጣህም?„ በማለት ጓደኞቼ ጠየቁኝ፡፡

„ጣራ ላይ ተሰቀለብኝ„ አልኳቸው፡፡ ሁለት እንጨቶች ቀጣጥዬ ለማውረድ ሞክሬ እንዳልተሳካልኝ ሁሉ ነገርኳቸው፡፡

„በድንጋይ ሞክረው!„ አለኝ አንዱ ጓደኛዬ፡፡

„እንደሱማ ማድረግ አልችልም፡፡ እናቴ ትቆጣኛለች!„ አልኩኝ እራሴን እየነቀነቅኩ፡፡



ከሁለት ቀናት በኋላ ከየት መጣ ሳይባል አንድ ቁራ ጣራችን ላይ አረፈ፡፡ ደስ በሚል ሁኔታ አየኝና ወደ ኳሱ ተመለከተ፡፡ ቀስ እያለ ወደ ኳሱ አቅጣጫ ሄደና በመንቁሩ ኳሱን ነካ ሲያደርገው በመደነቅ ተመለከትኩት፡፡ ኳሱ በቀላሉ ከጣራው ላይ እየተንከባለለ ወደ እኔ መጣ፡፡ መሬት ላይ እንዲያርፍ አልፈለኩም፡፡ እንደ አንድ ለአጭር ጊዜ ከቤተሰቡ ርቆ እንደተመለሰ ወንድም እቅፍ አደረግኩት፡፡ ተደስትኩ፡፡



„አመሰግናለሁ!„ አልኩት መልካሙን ቁራ፡፡ በአነጣጣሪው አይኑ ተመለከተኝና አንገቱን ነቅነቅ አደረገ፡፡ ሊረዳኝ ፈልጎ እንደመጣ አምኛለሁ፡፡ እናም ላመሰግነው ይገባል፡፡

# የተረሳው ጭቅጭቅ

ከየዝና ወርቁ

ፈንዲቃ ተብላ በምትጠራ መንደር ውስጥ ብርቱካን፣ አስናቀች፣ ደብሪቱ፣ ታደለች እና መብራቴ የሚባሉ ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር ይኖራሉ፡፡ አምስቱም በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ ፈንዲቃ የተለያዩ አበቦች በብዛት አስጊጠዋታል፡፡ አብዛኛው መሬትም በአረንጓዴ ሳር ስለተሸፈነ የመንደሩ ልምላሜ ያስደስታል፡፡ ብዙ ጊዜ ተስማምተው ይጫውታሉ፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ አይስማሙም፡፡ ዛሬ ያልተስማሙብት ቀን ነው፡፡

“ገመድ ዝላይ ነው መጫወት የምፈልገው” አለች ደብሪቱ፡፡

“እሱን ትላንት ተጫውተናል!›› እኔ ዛሬ የምፈልገው ድብብቆሽ መጫወት ነው!” አለች አስናቀች፡፡

“እኔ ደግሞ ቅልልቦሽ እንድንጫወት ነው የምፈልገው” አለች ብርቱካን፡፡ ታደለችና መብራቴ ደግሞ ምንም አላሉም፡፡ አምስቱም ዝም ብለው ተፋጠጡ፡፡

“መጀመሪያ ቅልልቦሽ እንጫወት፣ ከዚያ በኋላ ገመድ ዝላይ እና አኩኩሉ እንጫወታለን” በማለት ታደለች አስታራቂ ሃሳብ አቀረበች፡፡

“መጀመሪያ የምንጫወተው ገመድ ዝላይ ካልሆነ እኔ አልጫወትም!” ደብሪቱ በቁጣ ተናገረች፡፡

“መጀመሪያማ ደብብቆሽ ነው የምንጫወተው!” አለች አስናቅች፡፡ ታደለች እና መብራቴ ግራ እስኪገባቸው ድረስ እንዲሁ ሲጨቃጨቁ ቆዩ፡፡

“ካልተስማማችሁ ሳንጫወት ጊዜው ማለፉ ነው!” በማለት መብራቴ ተናገረች፡፡

“እኔ አንድ ሃሳብ አለኝ፡፡ ገመድ ዝላይ ትላንት ተጫውተናል፡፡ አሁን መጀመሪያ ድብብቆሽ እንጫትና ሲደክመን ቁጭ ብለን ቅልልቦሽ እንጫወታለን” አለች ታደለች፡፡

“አዎ ታደለች ልክ ነች” ተባባሉ፡፡ ታደለች ብዙ ጊዜ ሀሳብ ስትሰጥ ነገሮችን ስለምታገናዝብ ይቀበሏታል፡፡ ሁሉም ተስማሙ፡፡ ወንዙ አጠገብ ወዳለው ሜዳ ሄዱ፡፡ እዚያ ብዙ ዛፎች እና ቁጥቋጦዎች ስላሉ ደስ እያላቸው መጫወት ጀመሩ፡፡ አንዷ ፈላጊ ትሆንና አራቱ ይደበቃሉ፡፡ እንደዚህ እያደረጉ ሲጫወቱ እንደቆዩ ተረኛ ፈላጊ የነበረችው ብርቱካን አስናቀችን ልታገኛት አልቻለችም፡፡

ጥሩ መደበቂያ አግኝታ የጠፋችባት ስለመሰላት በጣም ፈለገቻት፡፡ እየቆየች ስትሄድ ግን ግራ ገባትና ለሁሉም ነገረቻቸው፡፡ ከዚያ ሁሉም ተበታትነው የአስናቀችን ስም እየጠሩ ይፈልጓት ጀመር፡፡ ግን ሊያገኟት አልቻሉም፡፡



ተጨነቁ፡፡ በዚህ ሁኔታ ጥቂት እንደቆዩ በድንገት የአስናቀችን ድምፅ ሰሙ፡፡

“አስናቀች! አስናቀች! አስናቀች!...“ እያሉና እየተሯሯጡ ድምፁን ወደሰሙበት አቅጣጫ ሄዱ፡፡

“እዚህ ነኝ!“ አለች አስናቀች፣ የጓደኞቿን ድምጽ ስትሰማ ደስታ እየተሰማት፡፡

“አስናቀች የቱጋ ነሽ?“ አሉ እየተሽቀዳደሙ በአንድ ድምጽ፡፡

“እዚህ ታች ነኝ፡፡ መውጣት አቃተኝ!“ አለች አስናቀች እያለቀሰች፡፡

ጉድባው ጫፍ ላይ ሆነው ወደታች ሲመለከቱ፣ አስናቀች በአንድ ጠባብ ቦታ ላይ ቁጢጥ ብላ ተቀምጣለች፡፡ ከዚያ በታች በርቀት ወንዙ ይታያል፡፡

“ለምን እዚህ ውስጥ ገባሽ?“

“አንሸራቶኝ!“

“አይዞሽ እኛ እናወጣሻለን“ አለቻት ታደለች፣ እየተቻኮለች፡፡

“ገመድ ያስፈልገናል“ አለቻቸው ብርቱካን፡፡ ደብሪቱና መብራቴ ግን ደንግጠው ስለነበር፡፡ ምንም አልተናገሩም፡፡

“በገመድ እናወጣታለን፡፡ በገመድ አስረው ከጉድጓድ ሲያወጡ አይቻለሁ፡፡ ችግር የለም“ አለቻቸው፡፡

“በገመድ ማውጣት ከቻልንማ እየሮጥኩ ሄጀ አመጣለሁ፡፡“ አለች ብርቱካን ጓደኛቸውን ማዳን እንደሚችሉ ስታስብ ድንጋጤዋ እየለቀቃት፡፡

“በእናታችሁ ቶሎ በሉ! ወንዙ ውስጥ እንዳልገባ ፈርቻለሁ!“ አለች አስናቀች እየተንሰቀሰቀች፡፡

“አይዞሽ! ተረጋጊ! አሁን እናወጣሻለን“ በማለት ታደለች አፅናናቻት፡፡ ከዚያም ደብሪቱና ታደለች ኮባ ቆርጠው አመጡ፡፡

ብርቱካን ገመዱን ይዛ መጣች፡፡ በጣም ስለሮጠች ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ነበር የደረሰችው፡፡ ታደለች ገመዱን ሸምቀቆ አሰረችውና አስናቀችን እንዳይጎዳት ዙሪያው ላይ የኮባ ቅጠሉን ጠቀለለችበት፡፡ ከዚያም ቀስ ብለው ወደ ገደሉ ጫፍ ቀረብ ብለው ቆሙ፡፡ ታደለች ገመዱን ለአስናቀች ወረወረችላት፡፡



“በክንዶችሽ ስር አስገቢው፤ ከዚያ እኛ እንጎትትሻለን“ አለቻት፡፡

አስናቀች እንደተባለው አደረገች፡፡ ታደለች በሆዷ ተኝታ ገመዱን መጎተት ጀመረች፡፡ ከኋላዋ ብርቱካን፤ ደብሪቱና መብራቴ በመደዳ ቆመው ገመዱን በመጎተት አንድ ላይ ተጋግዘው አስናቀችን ከገደል አወጧት፡፡

አስናቀች ከገደሉ እንደወጣች ከጓደኞቿ እቅፍ ውስጥ ገባች፡፡

“እዚህ በመደበቄ የሞኝ ስራ ነበር የሰራሁት፡፡ ስላገኛችሁኝ በጣም ነው የተደስትኩት፡፡ በጣም አመሰግናለሁ!“ አለቻቸው፡፡

“አስናቀች አንደኛ!“ አለች ብርቱካን ከኋላዋ ሆና እየሳቀች፡፡ ሌሎቹ ግራ ገባቸው፡፡ ትንሽ ቆይተው ግን ብርቱካን ቆጣሪ እንደነበረች ትዝ ሲላቸው እነሱም ሳቃቸውን ለቀቁት፡፡ እነ ደብሪቱ ቤት እስኪደርሱ ድረስ እየሳቁ ነበር፡፡

እዚያ እንደደረሱ ለብዙ ሰዓታት እያወሩ ግቢው ውስጥ ተቀመጡ፡፡ በጨዋታ



ምርጫ ላይ የተጨቃጨቁትን ረስተውታል፡፡ የሚዋደዱ ጓደኞሞች በመሆናቸው ደስተኞች ናቸው፡፡

# የሚሹ ድመት

ከውድአላት ገዳሙ

ሁልጊዜ ሚሹ ከትምህርት ቤት ስትመጣ ዶዮ ከበር ትጠብቃታለች። ሚሹ ገና ከበር ከመድረሷ „ሚያው!“ ትልና እግሯ ስር ትንከባለላለች። ሚሹ ብድግ አድርጋ ስታሻሻት ዶዮ ደስ ይላታል።

ዛሬ ግን እንደተለመደው ዶዮ ሚሹን ከበር አልተቀበለቻትም።

በዚህ አጋጣሚ ሚሹ ተረበሸች። ቀጥላም „ዶዮ! የት ነሽ? የት ተደብቀሽ ነው? „በማለት ሚሹ ደጋግማ ተጣራች ግን ምንም መልስ አላገኘችም። ሚሹ በቤታቸው ውስጥ ሁሉም ቦታ ዶዮን ፈለገቻት።



„እማዬ! ዶዮን አይተሻታል?“ አለቻት።

„ኸረ አላየኋትም! ግን አታስቢ አሁን ካለችበት ትመጣለች!“

„ግን እኮ ከትምህርት ቤት ስመጣ ሁሌ በሩጋ ትጠብቀኝ ነበር፤ ዛሬ ግን አላገኘኋትም!“ አለችና ሚሹ ማልቀስ ጀመረች።

„አይዞሽ አትጨነቂ ሚሹ። መጀመሪያ ምሳሽን ብዪ፤ ከዚያ አብረን ዶዮን እንፈልጋታለን። ለቅሶሽንም አቁሚ!“ በማለት እናቷ አባበሏት።



„እንዴ እማዬ በመጀመሪያ ዶዮን ማግኘት አለብኝ! ደግሞም አሁን የምግብ ፍላጎት የለኝም፤ አልራበኝም!“ አለች ሚሹ ።

„እስቲ ባቢ አይቷት እንደሆነ ጠይቂው። ቅድም ከበድሉና ከዳንኤል ጋር ኳስ ሲጫወቱ ነበር።“ በማለት እናቷ ነገሯት።

ሚሹ „እሺ!“ ብላ ሄደች።

ሚሹ ወደ መኝታ ክፍል ስትገባ ባቢ ክፍሉ ውስጥ አልጋው ላይ በሆዱ ተኝቶ ስዕል እየሳለ ነበር።

„ባቢ በእናትህ ዶዮን አይተሃታል?“ ሚሹ በፍርሃትና በጭንቀት ወንድሟን ጠየቀችው።

„አንቺጋ ነበረች እኮ፤ ማለቴ አንቺ ክፍል የለችም?“ ባቢ የድንጋጤ ስሜት ይታይበታል።

„ጠፋች እኮ! እቤት ውስጥ ሁሉም ቦታ ፈልጌያታለሁ፤ምንም ቦታ አልቀረኝም... „ አለችና እንደገና አለቀሰች።

„ውይ... በጣም አዝኛለው ሚሹ፤ አይዞሽ በቃ አታልቅሺ!“ አላት ባቢ ቀና ብሎ የሚስለውን ስዕል አቋርጦ እየተቀመጠ።

„ምናልባትምኮ ዶዮ ከቤት ወጥታ መንገድ ተሳስታ መመለስ አቅቷት ሊሆን ይችላል።“ ብላ ሚሹ ተንሰቀሰቀች።

„አልጠፋችም... ዶዮን እኔ አገኛታለሁ... አገኛታለው አይዞሽ ሚሹ... ! „ አለ ባቢ እህቱን እያቀፋት።

„ባቢ ዶዮን አይተሃታል ማለት ነው? እሺ ንገረኝ የት ነው ያለችው?“ ባዘነ ድምጽ ጠየቀችው።

„ነይ!“ አለና ባቢ እህቱን እየጎተተ ወደ ጓሮ ሄዱ። ሚሹ ድመቷን ለማግኘት በጣም ስለጓጓች ባቢን ተከትላው አብራው ወደ ጓሮ ሄደች ።

ከዚያም ሚሹ እናቷ ቆሻሻ ልብስ ከሚያስቀምጡበት ቅርጫት ውስጥ „ ሚያው!“ የሚል የዶዮን የሚያቃስት ድምጽ ሰማች። ቅርጫቱ እስከዛሬ ተከድኖ አያውቅም ነበር። አሁን ግን ሰፌድ ተከድኖ እላዩ ላይ ደግሞ ድንጋይ ተጭኖበት ነበር። ሚሹ በፍጥነት ድንጋዩን አነሳችና ክዳኑን ከፈተችው። ዶዮ ቆሻሻ ልብሶቹ መሃል ላይ ቁጭ ብላ ትቁለጨለጫለች።

„ማነው እዚህ ውስጥ የዘጋብሽ?“ አለቻት አውጥታ አሻሸቻት።



„ሚሹ ይቅርታ፤ ክፋት አስቤ አልነበረም። ቅድም ከዳንኤል እና ከበድሉ ጋር ጓሮ ኳስ ስንጫወት ዶዮ እየረበሸች ስላስቸገረችን ነበር እዚህ የከተትናት...“ በማለት መልስ መስጠት ጀመረ ባቢ።

„እና እንድትሞት ቅርጫት ውስጥ አስገብተህ ዘጋህባት?“ ሚሹ በወንደሚ በጣም ተናደደች።

„አዎን !... ግን እንድትሞት አልነበረም። የዶዮን ረብሻ ለማቆም ብቻ ነበር ድርጊቴ... ይቅርታ ሚሹ!“ አለ ባቢ በጥፋቱ ተፀፅቶ እየተመለከታት።

„ለምን ጨዋታችሁን ስትጨርሱ አልከፈታችሁላትም? እረሳሃት? „

„አዎን! ይሄም ጥፋቴ ነው... ሁለተኛ እንደሱ አላደርግም!“ በማለት ዶዮን እያሻሸ ተናገረ። ሚሹ ወንድሚ ጥፋቱን በማመኑ ከንዴቷ በረድ አለች።

„እሺ ሌላ ጊዜ ዶዮን ላለመጉዳት ቃል ትገባለህ?“ ስትል ሚሹ ወንድሚን ጠየቀችው።

„እንዴ! አዎ ቃል እገባለው ሚሹ፤ በፍፁም ሁለተኛ እንደዚህ አላደርግም! „አለ። በዚህ ተስማምተው ሁለቱም አብረው ወደ ቤት ገቡ።

ሚሹ ዶዮን እንዳቀፈቻት ከባቢ ጋር ወደ ቤት ሲገቡ እናትየው ደስ አላቸው ።

„ጎሽ የት አገናኛችኋት?“ አሏቸው የዶዮን አንገት እያሻሹ። ሚሹ እና ባቢ



ዶዮን የት እንዳገኟትና በምን ሁኔታ እንደነበረች ለእናታቸው ነገሩ። ባቢ አሁንም በመፀፀት ዳግመኛ ዶዮን እንደማይዘጋባት ቃል ገባ። „እማዬ ለዶዮ የሚሆን ወተት አለሽ? ሳይርባት አይቀርም፤ ከዘጋባት እኮ ረዥም ጊዜ ሆኗል“ አለች ሚሹ ።

እናትየውም ወተት ሲያወጡ ባቢ የዶዮን የመመገቢያ ሳህን አመጣ። ሚሹ የዶዮን ሳህን በወተት ሞላችው። ዶዮ በጣም እርቧት ስለነበር እያለከለከች መጠጣት ጀመረች። ስትጠግብ አፏን በሚሹ እና በባቢ እግሮች ላይ ማሻሸት እና መጠራረግ ጀመረች። ቤተሰቡ በዶዮ መገኘት ደስ ብሎት አመሸ።

# ከረሜላዬ

ከሣምራዊት አርአያ

አጎቴ በየሳምንቱ ቅዳሜ ቅዳሜ እቤታችን ይመጣል፡፡ ሲመጣ ከረሜላ ስለሚያመጣልኝ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ አንድ ቀን ያመጣልኝ አረንጓዴ ደስታ ከረሜላ ነበር፡፡ በጣም በጥድፊያ የከረሜላውን መጠቅልያ ልጩ አፌ ውስጥ ከተትኩት፡፡ አቤት እንዴት ይጣፍጣል፡፡

„ልጆች ምሳ ቀርቧል! እጃችሁን ታጥባችሁ ቅረቡ“ አለች እናታችን ከረሜላውን ገና ማጣጣም ስጀምር፡፡ ምን ባደርግ ይሻለኛል? እኛ ቤት ሁለት ሕጎች አሉ፡፡



• ሕግ ቁጥር አንድ፣- የቤተሰቡ አባላት በሙሉ ቅዳሜና እሁድ የምንመገበው በአንድ ላይ ነው፡፡

• ሕግ ቁጥር ሁለት፣- እኔ በዚህ ቅዳሜ ያፈረስኩት ነው፡፡ ከረሜላ ቸኮላት ወይም ሌሎች ጣፋጭ ነገሮችን ከምግብ በፊት መብላት የተከለከለ ነው፡፡

„ምን ነካኝ እንዴት ምሳ ሰዓት ላይ ከረሜላ አፌ ውስጥ አደርጋለሁ?“ ብዬ አሰብኩ፡፡

ደግነቱ የከረሜላውን መጠቅለያ በእጄ ይዤው ስለነበር ከረሜላዬን ከአፌ አውጥቼ መልሼ ጠቀለልኩት፡፡ ከዚያ „የት ላስቀምጠው?“ ብዬ አሰብኩ፡፡



የለበስኩት ልብስ ኪስ የለውም፡፡ በእጄ እንዳልይዘው ስበላ አይመቸኝም፡፡ ደግሞም እህትና ወንድሞቼ እንዳይበሉብኝ መደበቅ አለብኝ፡፡

ስለዚህ ወደ ቤት ከመግባቴ በፊት ቀስ ብዬ ማንም ሳያየኝ በሁለት ትላልቅ ድንጋዮች መሐል አስቀመጥኩት፡፡ ከዚያም ያለሃሳብ ወደ ምሳ ሄድኩ፡፡

ምሳዬን መቼም መብላት አይበለው፣ በጥድፊያ ጎረስ ጎረስ አደረግኩ፡፡ ወደ ከረሜላዬ ለመሄድ ስለቸኮልኩ ቶሎ ጠገብኩ፡፡

ከገበታ እንደተነሳሁ እጄን ታጥቤ በሩጫ ወደ ከረሜላዬ ሄድኩ፡፡ ያስቀመጥኩበት ቦታ አገኘሁት፡፡ በጣም ከመቸኮሌ የተነሳ ልጩ በቀጥታ አፌ ውስጥ ጨመርኩት፡፡ ለማየት እንኳን ጊዜ አልነበረኝም፡፡ ከረሜላው በጣም መረረኝ፡፡ በፍፁም ቅድም የቀመስኩት ከረሜላ አልመሠለኝም፡፡ እንደዚህ የሚመር ነገር በልቼ አላውቅም፡፡ ደግሞም አፌን ኮሰኮሰኝ፡፡ ወዲያውኑ እጄ ላይ ተፋሁት፡፡

ከረሜላዬ ላይ ብዙ ቁጫጮች ይርመሰመሳሉ፡፡

ከረሜላውን መልሼ ድንጋይ ላይ አስቀመጥኩትና ቁጫጮቹ ከረሜላዬን እየበሉ ሲዝናኑና ሲደሰቱ ቁጭ ብዬ አየኋቸው፡፡ ለካስ ቁጫጮችም እንደኔ ከረሜላ ይወዳሉ፡፡

# ቀበሮ ለምን የጫካ አይጥ እንደሚበላ

ከበቀለች ቶላ

የዝናብ ወቅት ነበር፡፡ ወንዙ ሞልቷል፡፡ ሰው ከሄደበት ተመልሶ ወንዙ አጠገብ ደርሷል፡፡ ሰው የሚኖርበት መንደር የሚገኘው ከወንዙ ማዶ ነው፡፡ ሰው እንዴት ብሎ ወንዙን መሻገር እንዳለበት ግራ ገብቶታል፡፡

“ተከተለኝ!“ የሚል ድምፅ ሰማ፡፡

“እንዴ! አንተ ቀበሮ! እኔን ልትረዳ? መቼም ቢሆን ለሰው ደህና ነገር አስበህ አታውቅም!“ አለው ሰው በጣም በመገረም፡፡

“እናንተ ሰዎችም ብትሆኑ እኮ ለእኛ መልካም ነገር አስባችሁ አታውቁም፡፡ ብዙ ትናንሽ ወንድሞቼን ገድላችሁብኛል!“ በማለት ቀበሮ መለሰለት፡፡

“እሱማ በጎቻችንን ስለምትበሉብን ነው!“

“እና ታዲያ ምን እንብላ?“ ሲል ቀነበሮ ጠየቀ፡፡

“አሁን መጣላት አያስፈልገንም፡፡ ወንዙን ካሻገርከኝ አንዱን በጌን እሸልምሃለሁ፡፡“ በማለት ሰው ተናገረ፡፡

ቀበሮ ተስማማና ከፊት ከፊት መሄድ ሲጀምር ሰው ተከተለው፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወንዙ በጣም ያልሞላበት ቦታ አገኙና አብረው ወንዙን ተሻገሩ፡፡

“አሁን ደግሞ ሽልማትህን እንድሰጥህ አንተ ተከተለኝ“ አለው ሰው፡፡

መንደሩ አጠገብ ሲደርሱ ሰው ቆመና “እዚህ ብትጠብቀኝ የሚሻል ይመስለኛል፡፡ ሌሎች የመንደራችን ሰዎች ካዩህ ያሳድዱሃል“ አለው፡፡

“ሽልማቴስ?“ ቀበሮ ተስፋ ቆርጦ ጠየቀ፡፡

“እሱንማ ይዤልህ እመጣለሁ“ በማለት አረጋጋው፡፡

ቀበሮ ተስማማና ከአንድ ጥቅጥቅ ካለ ቁጥቋጦ ኋላ ተደበቀ፡፡ ሰው ወደ መንደሩ ገባ፡፡

“እዚህ ምን ትሰራለህ?“ ሲል አጠገቡ ሲያልፍ የነበረ አንድ ሌላ ቀበሮ ቀበሮውን ጠየቀው፡፡

“ሰውን እየጠበቅኩ ነው፡፡ ወንዙን እንዲሻገር እረድቼው ነበር፡፡ እናም በግ ሊሸልመኝ ነው፡፡“

“አመንከው?“

“ለምን አላምነውም?“

“አባቶቻችን ‘ለሰው ሞት አነሰው’ እያሉ የሚነግሩንን እረሳኸው? እዚህ ሆነህ ቃል የተገባልህን በግ ስትጠብቅ ሰው አሳዶ ይዞ የሚገልህን ውሻ ይልክብሃል፡፡ ይልቅ ተነስና ከዚህ አካባቢ እንጥፋ!“ አለው ሌላኘው ቀበሮ፡፡



“ግዴለህም እንቆይና ከሁለታችን ማን ልክ እንደሆነ እንይ፡፡ ሰው ውሻ ይዞ ከመጣ ከሩቁ አይተን ሮጠን ማምለጥ እንችላለን“ በማለት ሌላው ቀበሮ መለሰለት፡፡

“ዛሬ ቀበሮ ወንዙን እንድሻገር ባይረዳኝ ኖሮ እዚህ አልገኝም ነበር፡፡ ለዚህ እርዳታው አንድ በግ እንደምሰጠው ቃል ገብቼለታለሁ፡፡“ ሲል ሰው ለእናቱና ለወንድሙ ነገራቸው፡፡

“ለቀበሮ አንድ በግ? ምን የማይረባ ነገር ነው የምትናገረው! ውሻውን ይዘህ ሂድና አባረው“ አለ ወንድሙ እራሱን እየነቀነቀ፡፡

“ለምን? ወዳጄ እኮ ነው፡፡ ወንዙን ያሻገረኝ እሱ እኮ ነው፡፡“

“ወዳጅንማ ማባረር ጥሩ አይደለም፡፡ ቢሆንም ግን በግ እንዳትሰጠው፡፡ ይልቅ ከዚህ አካባቢ እንዲሄድ ንገረው፡፡ እና ሰዎች በጎቻችንን ለመጠበቅ ስንል ቀበሮ፣ ነብርና ሌሎች ተመሳሳይ እንስሳትን እንገድላለን፡፡ እንደዚህ ከቀጠለ ደግሞ ቀበሮዎቹ ሞተው ያልቃሉ፡፡ ባይሆን ወደ ባሌ ተራራ እንዲሄድ ንገረው፡፡ ዘመዶቹ የሆኑት ቀይ ቀበሮዎች የሚኖሩት እዚያ ነው፡፡ ልክ እንደ ቀይ ቀበሮዎቹ የጫካ አይጦችን እየተመገበ መኖር ይችላል፡፡“ አሉ አስካሁን ዝም ብለው የነበሩት እናቱ፡፡



ይህን ተናግረው ሲያበቁ ሰውና ወንድሙ ቀበሮው ወዳለበት ቦታ ሄዱ፡፡

“ሁለት ሆነን መጣን፣ እናንተም ሁለት ሆናችሁ ጠበቃችሁን“ አለ ሰው ለቀበሮዎቹ፡፡

“ቃል የተገባልኝ በግ የታል?“ ሲል ቀበሮ ጠየቀ፡፡

“ጓደኛዬ ስለሆንክ በጉን ይዤልህ አልመጣሁም፡፡ ግን ጥሩ ምክር አምጥቼልሃለሁ“ አለው ሰው፡፡

“ምን አይነት ጓደኝነት እባክህ? ለነገሩ ከሰው ምን ይጠበቃል?“ ሁለተኛው ቀበሮ ንቀት በተሞላበት ሁኔታ ተናገረ፡፡

“ተረጋጋ! እኛ ሰዎች ኑሯችን የተመሰረተው በበግ ርቢ ነው፡፡ በጎቻችንን የምትበሉ ከሆነ ሰዎች እያደኑ ይገድሏችሁና ዘራችሁ ይጠፋል“ በማለት ሰው ተማፀነ፡፡

“እና ምን ይሻላል ትላላችሁ፣ ምን እናድርግ?“ አሉ ቀበሮዎቹ፡፡

“ወደ ባሌ ተራራ ውጡ፡፡ እዚያ የወንድማችሁ ልጅ ቀይ ቀበሮ አለ፡፡ ልክ እንደሱ እዚያ ያሉትን ብዛት ያላቸውን የጫካ አይጦች በመመገብ መኖር ትችላላችሁ፡፡“

ሁለቱ ቀበሮዎች ተነጋገሩና ተስማሙ፡፡ ባሌ ተራራ የት እንደሚገኝ ስላላወቁ በዚያ በኩል በአጋጣሚ ሲያልፉ የነበሩ የኒያላ ወንድሞች፣ ድኩላ እና ከርከሮ እንደሚገኙ ወንድምየው ነገራቸው፡፡

“ወደ እዚህ እየመጣን እያለ ዛፍ ስር አረፍ ብለው አይቼያቸኋለሁ፡፡ ኑ! የት እንዳሉ እናሳያችኋለን፡፡ እነሱን ተከትላችሁ ከሄዳችሁ ባሌ ተራራ ትደርሳላችሁ“ አላቸው፡፡

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ቀበሮ ባሌ ተራራ ላይ እንደ ወንድሙ ልጅ ቀይ ቀበሮ የጫካ አይጥ እየተመገበ መኖር ጀመረ፡፡





በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ታሪኮች፤ለኢትዮጵያ ህጻናት መጽሐፍ ደራሲያን በአዲስ አበባ ጎተ ኢንስቲትዩት በ2004 ዓ.ም በጀርመን ኢራናዊቷ የልጆች መጽሐፍ ደራሲ ናስሪን ዚገ አማካኝነት ከተሰጠ ወርክሾፕ በመነሳት የተጻፉ ናቸው፡፡

GOETHE INSTITUT

Art of Buna